ስለ ትምህርት ሥርዓታችን

በ ሐያው

by hiyaw nrs

no 0938026253

@ahune

- በሀገራችን ኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ የትምህርት ተቋማት (ከቅድመ መደበኛ _ ዩኒቨርስቲ) ፣ የተማሪ ፣ የመምህራን ቁጥር በጥቅሉ በትምህርት ዘርፉ ላይ የቁጥር እድገት ቢኖርም በጥራት በኩል የተወሰኑ ክፍተቶች ይስተዋላሉ። ከነዚህም ውስጥ ካለፍኩበት ና ከነባራዊ ሁኔታ በመነሳት የሚከተለውን አስፍራለሁ።

1ኛ የቅድመ መደበኛ ትምህርት አለመስፋፋት

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ልጆች ከቤት ወደ ት/ቤት የሚሸጋጋሩበት ጊዜ ነው። በሌላ ቋንቋ ከመኖሪያ ቤታቸውና ከወላጆቻቸው (ከለመዱት ዓለም) ወደ ትምህርት ቤትና ጓደኞቻቸው (አዲሱ ዓለማቸው) የሚሸጋገሩበት ጊዜ በመሆኑ በት/ቤት ቆይታቸው ሳይደብራቸው ና ሳይሰላቸቸው ለመደበኛ ትምህርት የሚዘጋጁበት እና የተለያዩ ክህሎቶቻቸውን የሚያዳብሩበት እርከን ነው።

... የቀጠለ

- በዚህ ቆይታቸው እንደየ ክፍል ደረጃቸው በግልም ይሁን በጋራ በመጫወት ፣ በመዘመር ፣ ስዕል በመሳል ፣ መጫወቻዎችን በመገጣጠም...ወዘተ አከላቸውን እና አዕምሮቸውን የሚያፍታቱበት ቀላል ያሉ ነገሮችን ያለ አጋዥ በራሳቸው ማድረግን የሚማሩበት መወሰንን የሚለማመዱበት እንዲሁም የነገሮችን አጠቃቀም የሚያውቁበት ወሳኝ ጊዜ ነው።

... የቀጠለ

- በመፃፍና በማንበብ የቋንቋ ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት እንዲሁም ቁጥር መቁጠርና ቀለል ያሉ መሰረታዊ የሂሳብ ስሌቶችን በመለማመድ የሂሳብ ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት ጊዜ ነው።
- የቅድመ መደበኛ ት/ትን መከታተል ከአካዳሚያዊ ዝግጅት በተጨማሪ በተማሪዎች ተነሳሽነት ፣ ጥረት ፣ ስነ-ስርዓትና ሕግ-አክባሪነት... ላይ በጎ ተፅዕኖ አለው። ስለዚህ ቅድመ መደበኛ ትምህርትን በተከታተለና ባልተከታተለ ልጅ /ተማሪ መካከል የረዥም ጊዜ ልዩነቶችም ይፈጠራሉ ማለት ነው።

... የቀጠለ

- ስለዚህ የቅድመ መደበኛን ት/ት መከታተል ለት/ት ጥራት ጉልህ አስተዋፅዖ ያበረክታል ማለት ነው። እንዳለ መታደል ሆኖ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዚህ በኩል በአፍሪካ ደረጃ እንኳን ወደኋላ እንደቀረች መረጃዎች ይጠቁማሉ።

2ኛ የተማሪና የክፍለ ጥምረታ

- እንደሚታወቀው ሀገራችን ገና ታዳጊ ሀገር በመሆኗ ት/ት በሚፈለገው ደረጃ አልተስፋፋም። በመሆኑም መንግስት ይህን ችግር ለማቃለል እና ለተማሪው ት/ትን ለማዳረስ በሚመስል በደረጃ በአንድ ክፍል ውስጥ ብዙ ተማሪዎችን በፈረቃ እያስተማረ ይገኛል። ነገር ግን ይህ ዓይነት የት/ት አቀራረብ ለተማሪውም ሆነ ለመምህራኑ ምቹ አይደለም። የት/ት ጥራትም እንዳይረጋገጥ እንቅፋት ይሆናል።

... የቀጠለ

- በአንድ ክፍል ውስጥ ብዙ ተማሪ ሲማር የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ይኖሩታል። ከነዚህም ውስጥ የተወሰኑትን እንጥቀስ ፦
- ተማሪው ያልገባውን ለመጠየቅ ፣ በተጠየቀ ጥያቄ ላይ መልስ ለመስጠት ወይም በክፍል ውስጥ መሳተፍን መፍራት
- በክፍል ውስጥ ተማሪ ፊት ቆሞ አቅርበት ለማቅረብ (ፕረዘንት ማድረግ) መፍራት
- መምህሩ የክፍል ና የቤት ስራዎችን ፣ፈተናዎችን፣ አሳይመንቶችን በየጊዜው ለመስጠትና ተማሪውን

... የቀጠለ

- የአቻ ግፊትና የስነልቦና ጫና ፦ ሁሉም ተማሪ አንድ ዓይነት አይሆንም ስለዚህ አንዱ አንዱ ላይ ተፅዕኖ መፍጠሩ የየማይቀር ጉዳይ ነው። እንደኛ ካልሆንክ እንደኛ ካላደረክ ከኛ ጋር አትውልም አብረከን አትሆንም የሚል ማግለል ስላለ አንድ ተማሪ ሳይወድ በግዱ እንደ ቡዱኑ ይሆናል።
- ዖታዊ ትንኮሳ ለማሳረፍ ፦ በአንድ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች በብዛትና ተፋፍገው የሚቀመጡ ከሆነ በተለይ ሴት ተማሪዎች ለለከፋ ወይም ለጉንተላ ይጋለጣሉ።

... የቀጠለ

- በአንድ ዴስክ ላይ ተማሪዎች ተጠጋግተው ስለሚቀመጡ ለመፃፍና የትምህርት ቁሳቸውን ለማስቀመጥ መቸገር
- በክፍል ውስጥ በቂ የመዘወሪያ ቦታ አለማግኘት ስለዚህ መምህሩ አንድ ቦታ ብቻ ቆሞ ለማስተማር መገደድ
- ለመማሪያ ክፍለ ወበቅ እና አለስፈላጊ ጠረን መፈጠርና በትንፋሽ ለሚተላለፍ በሽታዎች (እንደ ጉንፋን) መጋለውስጥ
- በማጅራት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በዚህ ሁኔታ ላይ

... የቀጠለ

- በፍሽን ፣ በሜካፕና መኳኳል ፣ በኪስ ሳንቲም ፣ በመላላጥ ፣ ሙድ በመያዝ ...ወዘተ ፉክክር ውስጥ መግባት በተለይ ሁለተኛ ደረጃ ና ከዛ በላይ ባሉ ተማሪዎች
- ከንቱ ለሆነ የሐይማኖት ፣ የፖለቲካና ለታሪክ ክርክር መጋለጥ
- ለቡድን ፀብና ጀብደኝነት መነሳሳት

... የቀጠለ

- ሥርቆትና ሌብነት መስፍፍት። በተለይም በደብተር ማርክ ጊዜ የተማሪዎች ደብተር መጥፋት
- እኝህን እና ሌሎች ያለተጠቀሱ ቸግሮቸን ያስከትላል በመሆኑም በተማሪው የት/ት አቀባበል እና በመምህሩ ተነሳሽነት ላይ አሉታዊ ጫና በማሳረፍ የት/ት ጥራት እንዲቀንስ ያድጋል። በሌላ አገላለፅ ተማሪው በሚማርበት የክፍል ደረጃ ማወቅ ያለበትን ያክል እያወቀ እንዳይሄድ በር ይከፍታል ማለት ነው።

3ኛ የፊረቃ ትምህርት

- ትምህርትን በፊረቃ ማድረስ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው። ለምሳሌ ተማሪዎች ተከታታይ ክፍለ ጊዜዎችን (ፔሬዶችን) ስለሚማሩ እንዲሰላቹ ይሆናል። የእረፍት ጊዜ /ሰዓት አጭር እንዲሆነ ያደርጋል፣ መምህሩ ሁሉንም የመፃህፍን ምዕራፎች ለመጨረስ ይቸገራል.... የመሳሰሉት ችግሮች ያጋጥማሉ። ትምህርትን ለመፎረፍም ያመቻል፣ ተማሪው ከቤት ወደ ት/ቤት መመላለስ እንዲሰለች ያደርጋል። ከነዚህ ሌላ ከላይ የጠቀስናቸው በአንድ

4ኛ የመምህራኑ ችሎታ

- ከመምህር መምህር በማስተማር በማስረዳት ምሳሌ በመጠቀም በተማሪ አያያዝ የክፍሉን ፀጥታ በመቆጣጠር የተማሪውን ትኩረት በመሳብ። የተማሪውን ችሎታ በመመዘን ሰዓት በማክበር የተማሪውን አቴንዳንስ በመቆጣጠር ማስተማር ያለበትን በጊዜው አስተምሮ በመጨረስ ለተማሪው ክለሳ በማድረግ በዝግጁነታቸው በተነሳሽነተቸው... ይለያያሉ።

5ኛ የወላጅ ድጋፍና ክትትል

- ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ት/ቤት ከላኩ በኋላ ልጆቻቸው ምን ተምረው እንደመጡ በየቀኑ ያለመጠየቅ /ያለመከታታል ችግር በብዙ ወላጆች ዘንድ አለ። ለዚህ ችግር ደግም የተለያዩ ምክንያቶች ይኖራሉ። ከነዚህም ውስጥ ወላጅ ልጁን በያስተምርም ለራሱ መማሩ አጠያያቂ ነው። ምክንያቱም በሀገራችን የትምህርት መስፋፋት የቅርብ ጊዜ ታሪክ ስላለው ነው።
- ወላጅ ኑሮን ለማሸነፍ በኑሮ ትግል ስለሚጠመድ

... የቀጠለ

- ሁሉም ወላጆች የት/ትን ጥቅም ያለመረዳት። በመሆኑም ልጆቻቸውን እስከሚቻሉት ድረስ ከማስተማር ይልቅ በቤት ውስጥ ና ከቤት ውጭ ባሉ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ወይም በለጋ እድሜያቸው ወደ ትዳር ዓለም እንዲገቡ በማደረግ ከህልማቸው የማጨናገፍ ችግርም ይስተዋላል።
- አንዳንድ ወላጆች ደግሞ ለልጆቻቸው የሚያደርጉት ድጋፍ ከልብ የመነጨ አለመሆን ማለትም ከኔ አይቅር ወይም በይስሙለ ዓይነት ስሜት ለልጅ ለትምህርት የሚያስፈልገውን ቁሳቁስ

... የቀጠለ

- ወላጆች ስራዬ ብለው ት/ት ቤት ድረስ በመሄድ ከልጆቻቸው መምህር ጋር አለመወያያት። ይህ መሆኑ ደግም ለተማሪ ስነ-ምግባር መበለሽት በር ይከፍታል። ወላጅ እና መምህር ስለተማሪው ቢወያዩ በጊዜው መስተካከል የሚችል ጉዳይ ስር ሰዶ መፈታት ወደ ማይችልበት ደረጃ እንዳይሻገር ያግዛል።

... የቀጠለ

- አንድ መምህር በክፍል ውስጥ ስለሚያስተምረው ተማሪ ከአካዳያዊ ጉዳይ በተጨማሪ በስነ-ምግባሩ ፣ ችሎታው ፣ ተሰጥአው ፣ የትምህርት አቀባበሉ ላይ ፣ ንፅህናው ላይ ፣ ከተማሪዎች ወይም ከክፍል ጓዳኞቹ ጋር ስላለው መስተገብር ...ወዘተ ጉዳዮች ላይ ትኩረት መስጠት አለበት። ምክንያቱም ልጅ/ተማሪ ልዩ ችሎታ ካለው እንዲያዳብር ወይም ችግር ካለበት ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ በጊዜው እንዲፈታ ትልቅ አስተዋፅኦ ያበርክታል።

6ኛ የትምህርት ቤቶች ሳቢ አለመሆን

- የሀገራችን ት/ቤቶች በራሳቸው ሳቢ አይደሉም። ብዙ ነገር ይጎድላቸዋል። ት/ቤቶቹ በየጊዜው የማይታደሱና ቀለማቸው የቆሸሸ ወይም የለቀቀ ፣ ኮርኒስ የሚጎድላቸው ፣ በር መስኮታቸው ያልታደሰ/ያረጀ ፣ መብራት በበቂ ሁኔታ የሌለባቸው ፣ በክፍል ውስጥ ግድግዳ ላይ ለትምህርት የሚጠቅሙ ስዕል አንደ ዓለም ካርታ ፣ ፔሬዲክ ቴብል.. ያልተለጠፈባቸው ፣ ጥቁር ሰሌዳው ና የተማሪው መቀመጫ ዴስክ በየጊዜው የማይቀየሩበት/ የማይታደሱበት ፣ የኾክ ብናኝ ተማሪውን የማረብሸበት ፣ ብዙ የክፍል ውስጥ ገፅታቸው ሳቢ

...የቀጠለ

- ማረፊያና መዝናኛ ክፍል ፣ የስፖርት ሜዳ ፣ በተማሪው ቁጥር ልክ የውሃና የመፀዳጃ አገልግሎት ፣ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ፣ የቤት መፃህፍት ና መፃሃፍ በራሱ ፣ የቤተ ሙከራ ክፍል ፣ የኮምፒውተርና የኢንተርኔት አገልግሎት ወይም አቅርቦት ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና ክፍልና ቁሳቁስ ፣ የስነ-ልቦና አማካሪና የማማከሪያ ክፍል የሚጎድላቸው ወይም እስከነአካቴው የማይኖራቸው ... ብቻ ብዙ ነገር ስለሚጎድላቸው ለተማሪው ሳቢ አይደሉም። ለመምህሩም እንደዘው። ስለሆነም ተማሪዎች ደስ ብሏ ቸው ትምህርት ቤት ውስጥ እንዳ ቆዩ

7ኛ የተግባር ልምምድ አለመዳበር

- የሀገራችን የትምህርት ሥርዓት ለፅንሰ-ሀሳብ እንጂ ለተግባር ልምምድ ብዙም ትኩረት ስለማይሰጥ ተማሪዎች ሳይንስ ነክ ትምህርቶች ላይ እንዳይሳቡ እና በክፍል ውስጥ የተማሩትን በተግባር አይተው በአዕምራቸው ተቀርፆ እንዳይቀር ያደርጋል። በመሆኑም ብዙ ተማሪዎች የሳይንስ ትምህርቶች ላይ እንዳይሳቡ በር ከፍቷል።

8ኛ ቋንቋ

- ትምህርቶች እንዲረሱና ዋና ሀሳባቸው በተማሪዎች ላይ ተቀርጸ እንዳይቀር ከሚያደርጉት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የቋንቋ ችግር ነው። ተማሪው እስከ 12ተኛ ክፍል ድረስ የእንግሊዘኛን ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት የሚወስድ ቢሆንም የቋንቋውን አራቱን መሰረታዊ ክህሎቶች ላይ ክፍተቶች ይስተዋላሉ። እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ጠቃሚ ቢሆንም ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ትምህርቶችን በእንግሊዝኛ መቀጠል

9ኛ ሳይንስ ነክ ታሪኮች

- በአሁኑ ጊዜ በትምህርት ዓለም ውስጥ ከታችኛው እርከን እስከ ከፍተኛው የትምህርት ተቋም ድረስ ያሉ የትምህርት ዓይነቶች ወይም የጥናት መስኮች በተፈጥሮም ይሁን በማህበራዊ ሳይንስ እንዲሁ በአንድ ጊዜ የመጡ አይደሉም። በብዙ ዓመታት (በሺ በሚቆጠር) በብዙ ፈላስፎች የፈጠራ ሰዎችና ተመራማሪዎች በተለያዩ ሁኔታዎች (በአጋጣሚዎች ና በምርምር) በተለያዩ ሀገሮች ቀስ በቀስ አንዱ የአንዱን ሀሳብ እየመረመረ በሂደት የተፈጠሩ መሆናቸው ይታወቃል።

... የቀጠለ

- በኛ ሀገር ስለዚህ ጉዳይ የሚያብራራ አጋዥ መፃህፍትን በባትሪ ፈልጎ ማግኘት በመርፌ ቀዳዳ የማለፍ ያክል ነው። ስለ ሳይንስ እድገት የሚተርኩ ኢ - ልቦለድ ጽሑፎች የተመራማሪዎች የሕይወት ታሪክ እስከነ ሥራቸው በጽሑፍ መልክ መቅረብ ተማሪዎች ወደ ዘርፉ እንዲሰቡ መነሳሳትን ይፈጥራል።

አመሰግናለሁ